Minnesota Department of Health (የሚኔሶታ የጤና መምሪያ)

# ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ ላለባቸው በሽተኞች እቤት ውስጥ የሚደረግ የመተንፈሻ ጥንቃቄዎች

---

**የታካሚው ስም:** ______________________ **የልደት ቀንና ዓ ም:** ___/___/___

**የአካባቢው የህዝብ የጤና ድርጅት፡** ______________________ **ስልክ:** (___)__________

**የቲቢ ሀኪም:** ______________________ **ስልክ:** (___)__________

**ከሀኪምዎ ጋር ያለው የሚቀጥለው ቀጠሮ፤** ______________________

**መረጃው ከታካሚው ጋር ያየው** ______________________ **በ(ቀን)** ___/___/___

ምርመራዎችዎ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊሰራጭ የሚችል የሳንባ ነቀርሳ ሊኖርብዎት እንደሚችል ያሳያሉ። አሁን ሆስፒታል መግባት የለብዎትም። ሀኪምዎ ቲቢን ለማከም መድኃኒት አዞ ሊሆን ይችላል። የጤና አጠባበቅ ሠራተኞች በእርስዎ ቤት እያሉ እራሳቸውን ለመከላከል ጭምብል ያደርጉ ይሆናል።

እርስዎ በህጻናት፣በወጣት ልጆች፣ወይም ከኤች አይ ቪ ወይም ከነቀርሳ የተነሳ ደካማ የሰውነት መቋቋሚያ ሁኔታ ባላቸው ሰዎች አጠገብ መሆን የለብዎትም። ምክንያቱም እነርሱ በሽታውን የመቋቋም አቅም ያንሳቸዋል። ዕድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች የሆነ ከርስዎ ጋር የሚኖሩ ልጆች ቲቢ እንዳላቸው በሀኪም ከተመረመሩ በኋላና በሳንባ ነቀርሳ እንዳይታመሙ ለመከላከል መድኃኒት እየወሰዱ ከሆነ ከርስዎ ጋር መቆየት ይችላሉ ።

የራስዎን የቲቢ ተውሳክ ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳይተላለፍ ለመከላከል ማድረግ ያለብዎት በጣም ጠቃሚ ነገሮች እናሆ፤

- በሚያስልዎ ወይም በሚያስነጥስዎ ጊዜ ሁል ጊዜ አፍዎንና አፍንጫዎን ይሸፍኑ። አንዳንድ ሰዎች ሙቅ ፈሳሾችን በሚጠጡበት ጊዜ በትንሹ ይስላሉ።
- እቤት እያሉ፣ እንደ ሽንት ቤት ወይም ኩሽና በመሳሰሉ ሌሎች ሰዎች በሚጠቀሙ ክፍሎች ለአጭር ጊዜ ብቻ ይቆዩ። እቤት ውስጥ ከርስዎ ጋር ከሚኖሩ የቤተሰብ አባላት ጋር አብረው ሲኖሩ ጭምብል ማድረግ አያስፈልግዎትም።
- ከጤና አጠባበቅ ሠራተኞች በቀር ጎብኚዎች ወደ ቤትዎ እንዲመጡ አይፍቀዱ። ሌሎች ሰዎችን ለመጎብኘት አይሂዱ።
- ከቻሉ፣ እቤትዎ እያሉ፣የአየር ማረገቢያ ወይም መስኮቶችን ይክፈቱ። ይህም አየር በአካባቢው እንዲዘዋወር ይረዳል። እርስዎ ከቤትዎ ውጭ በክፍት ሥፍራ ያለ ጭምብል መሄድ ይችላሉ።
- በቀጥታ የሚታይ ህክምና ((Directly Observed Therapy (DOT)) TBዎን ለማዳን ምርጥ ዘዴ ነው። ሀኪምዎና የህዝብ ጤና ጥበቃ ነርስ ስለ DOT በተመለከተ ይነግሩዎታል። የህዝብ ጤና አጠባበቅ ሠራተኛ የTB መድኃኒትዎን እያመጠልዎት መውሰድዎን ያያል። ስለ ቲቢ መድኃኒትዎ በተመለከተ ማንኛቸውም ጥያቄዎች ወይም ችግሮች ካሉ ለጤና አጠባበቅ ሠራተኛዎ ለመንገር እርግጠኛ ይሁኑ።
- ወደ ሥራ፣ ት/ቤት፣የአምልኮዎ ሥፍራ፣ ቤተ መጻህፍት፣ ወይም ሱቅና የፖስታ ቤት ወደ መሳሰሉ የህዝብ ቦታዎች አይሂዱ።
- አውቶቡሶችን፣ታክሲዎችን፣ ባቡሮችን፣እና አይሮፕላኖችን ጨምሮ የህዝብ ማመላለሻዎችን አይጠቀሙ።
- ወደ ሁሉም የህክምና ቀጠሮችዎ ይሂዱ። ሀኪምዎ ምርመራ አድርግልዎት የቲቢ መድኃኒትዎ መሥራትዎን ያረጋግጣል። በቀጠሮ ካልተገኙ ፣ቲቢዎን ለማዳን ረጅም ጊዜ ሊፈጅ ይችላል።
- ሀኪምዎ ወይም ነርስዎ ልዩ ጭንብል ይሰጥዎታል። ወደ ሆስፒታል ወይም ክሊኒክ በሚሄዱበት ጊዜ ይህን ጭንብል ያድርጉ።
- ሀኪምዎ ወይም የህዝብ ነርስዎ ጭንብልዎን ትተዎ ወደ ዳህና ሥራዎቹዎ እንድመለሱ ዘንድ ይነግሩዎታል።

ስለ ቲቢ ወይም ስለ ህክምናዎ ጥያቄዎች ቢኖሩብዎ ሀኪምዎ ወይም የህዝብ ነርስዎን ያነጋግሩ።

**ይህ ጽሁፍ የተወሰደው ከ፤** New York City Department of Health. Hospitalization and Community Discharge of TB Patients Protocol in Clinical Practices Manual, 2004.

**ዋቢ መጽህፍት፤** Centers for Disease Control and Prevention (የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከላት)። Guidelines for Preventing the Transmission of *Mycobacterium tuberculosis* in Health-Care Settings, 2005. MMWR 2005; 54(No. RR-17): [38, 45].

Centers for Disease Control and Prevention (የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከላት)። Controlling tuberculosis in the United States: recommendations from the American Thoracic Society, CDC, and the Infectious Diseases Society of America. MMWR 2005; 54(No. RR-12): [28].

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH

Tuberculosis Prevention and Control Program
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
1-877-676-5414, 651-201-5414
www.health.state.mn.us/tb